የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 656/2013

ህዳር 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ·

መግቢያ

የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን ሳይኖራቸው በመንገድ ላይ ሲነዱ ወይም ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚችሉ ተሽከርካሪዎች በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ካሳ የሚከፍሉበት ሁኔታ፣ተደጋጋሚ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎችና አሽከርካሪዎች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ፣ ከአንድ አመት ላነሰ ጊዜ የሚሰጥ የመድን ፖሊሲ የውል ዘመኑን መሰረት ያደረገ የመድን ምስክር ወረቀትን በተመለከተ እና ሌሎች የአሰራር ዝርዝር ሊቀመጥላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎች በማስቀመጥ የአዋጁን አፈጻጸም የተሻለ ማድረግ በማስፈለጉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን የመድን ውል እና የካሳ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 656/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. በአዋጅ ቁጥር 799/2005 የተተረጎሙት ቃላት ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. "አዋጅ" ማለት የ3ኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 ነው፤
3. "ደንብ ማለት" የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 300/2006 ነው፤
4. "ኤጀንሲ " ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 300/2006 የተቋቋመው የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
5. "የመድን ተለጣፊ" ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረት ለተሽከርካሪ አደጋ የ3ኛ ወገን መድን የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመኪና የፊት መስታወት ላይ የሚለጠፍ ወይም የፊት መስታወት ለሌላቸው ተሽከርካሪዎች በአሽከርካሪው እጅ ሚቀመጥ ሰነድ ነው፤

6. "የአደጋ መመዝገቢያ ቅፅ" ማለት በአንድ መድን በተገባለት ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን ውሉ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ የተመዘገበ የጉዳት ብዛት የሚያሳይ ቅጽ ነው፤
7. "መድን ያልተገባለት ተሽከርካሪ" ማለት በአዋጁ መሰረት የጸና የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የሌለው ተሽከርካሪ ወይም የኢንሹራንስ ሽፋን ቢኖረውም የመድን ሽፋኑን የሰጠው የመድን ኩባንያ በመክሰሩ ምክንያት ካሳ ለመክፈል አቅም ያጣ ተሽከርካሪ ነው፤
8. "ያልታወቀ ተሽከርካሪ" ማለት አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ እና አሽከርካሪው እና ባለንብረቱ ያልታወቀ ተሽከርካሪ ነው
9. "የሆስፒታል ሕክምና ወጪ" ማለት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በህክምና ተቋም ውስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት ሲታከም የወጣ የህክምና ወጪ ሲሆን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወጪን አያካትትም፤

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኤጀንሲው ፣ በመድን ሰጭ ፣ በመድን ገቢዎች እንዲሁም በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት በደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ።

ክፍል ሁለት
የመድን ምስክር ወረቀትና ተለጣፊ ዝግጅት እና አሰጣጥ

4. የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ዝግጅት

1. ኤጀንሲው የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲኖራቸው በአስገዳጅነት ለተደነገገባቸው ተሽከርካሪዎች የሚያገለግል አንድ አይነት የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ያዘጋጃል።
2. ኤጀንሲው ለመድን ሰጭ የሰጠውን የመድን ተለጣፊ እና የመድን ምስክር ወረቀት አጠቃቀምን በተመለከተ ቁጥጥር እና ክትትል የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
3. በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ የሚታተም እያንዳንዱ የመድን የምስክር ወረቀት አንድ ዋና እና አንድ ኮፒ ይኖረዋል።
4. በኤጀንሲው የሚታተሙ የመድን ምስክር ወረቀቶች በሙሉ ተከታታይ የሆነ ቁጥር ይኖራቸዋል።

Ministry of Transport

5. በእያንዳንዱ የመድን ምስክር ወረቀት ላይ የመድን ውል ቁጥር እና የመድን ምስክር ወረቀቱ የመዝገብ ቁጥር የሚጻፍበት ክፍት ቦታ ይኖረዋል፡፡ የመድን ሰጭው ክፍት ቦታው ላይ በኮምፒዩተር መጻፍ አለበት፡፡
6. የመድን ምስክር ወረቀት በአዋጁ አንቀጽ 9 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
7. ልዩ የሕትመት መለያ ምልክት በሁሉም የመድን ምስክር ወረቀት ገፆች ላይ በጉልህ መታየት አለበት፡፡
8. የመድን ተለጣፊ ክብ ቅርፅ ያለው ሆኖ የሚዘጋጅ ሲሆን ባለ ሁለት ክብ መስመሮች መሀል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የሚል ጽሁፍ በጉልህ ይገኝበታል፡፡
9. እያንዳንዱ የመድን ተለጣፊ ልዩ ምልክት፣ ጎልቶ የሚታይ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበትን ዓመት ለመፃፍ የሚያስችል ባዶ ቦታ ያለው ሆኖ ይዘጋጃል፡፡
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ከተገለጸው በተጨማሪ የመድን ተለጣፊ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል ፤

    ሀ. የተሽከርካሪው የሰሌዳ ቁጥር

    ለ. የመድን ምስክር ወረቀት ቁጥር

    ሐ. የውል ዘመን

    መ. የተሽከርካሪው የመጫን አቅም በሰው እና በኩንታል

    ሠ. የመድን ሰጭው ስምና አድራሻ

    ረ. የመድን ሰጭው ማሕተም

5. የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ አሰጣጥ

ማንኛውም መድን ሠጭ የመድን ምስክር ወረቀት እና ተለጣፊ ሲሰጥ የሚከተሉትን ዝርዝር የሥራ መመሪያዎች ማክበር አለበት፡-

1. ማንኛውም መድን ሰጭ የሚሰጠው የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ በዚህ መመሪያ መሠረት በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ የሚሰራጨውን ብቻ ነው፡፡
2. ማንኛውም መድን ሰጭ ለመድን ገቢው ከመድን ውሉ ጋር በአባሪነት የመድን ምስክር ወረቀትና የመድን ተለጣፊ መስጠት አለበት፡፡

3. ማንኛውም መድን ሰጭ መድን ለተገባለት ተሸከርካሪ የሰጠውን የመድን ምስክር ወረቀትና የመድን ተለጣፊ ዝርዝር ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት ለኤጀንሲው መላክ አለበት፡፡
4. ማንኛውም መድን ሰጭ በመድን ምስክር ወረቀት ላይ ሊካተቱ የሚገባቸው መረጃዎችን በሙሉ በግልጽ እና በአግባቡ መጻፍ አለበት፡፡
5. አንድ የምስክር ወረቀት የሚዘጋጀው ለአንድ ተሸከርካሪ ብቻ በመሆኑ ማንኛውም መድን ሰጭ ለሌላ ተሸከርካሪ ማስተላለፍ የለበትም፡፡
6. ማንኛውም መድን ሰጭ ለእያንዳንዱ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ አንድ የራሱ የሆነ የመድን ምስክር ወረቀት መስጠት ያለበት ሲሆን የመድን ምስክር ወረቀት የሚሠጠውም የመድን ሽፋን ውል በሰጠው መድን ሰጭ ኩባንያ ብቻ ነው፡፡
7. ማንኛውም መድን ሰጭ በሚሰጠው የመድን ተለጣፊ እና የመድን ምስክር ወረቀት ላይ የሚጻፍ መረጃ እና መግለጫ በሙሉ በኮምፒዩተር መጻፍ ያለበት ሲሆን ምንም ዓይነት ስርዝ ድልዝ ወይም ማስተካከያ በላዩ ላይ መታየት የለበትም፡፡፡
8. ማንኛውም መድን ሰጭ ለሚሰጠው አንድ የመድን ምስክር ወረቀት አብሮ የሚሄድ አንድ የመድን ተለጣፊ መስጠት ያለበት ሲሆን የመድን ተለጣፊው የሚፀናበት ጊዜም ከተሰጠው የመድን ምስክር ወረቀት ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን አለበት፡፡
9. ማንኛውም መድን ሠጭ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የመድን ምስክር ወረቀት ላይ የመድን ሰጪዉን ማህተም ማድረግ አለበት፡፡
10. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መድን ሠጭ የሚሰጠው የመድን ምስክር ወረቀት የሚጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

6. የመድን ውል ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1. የመድን ውል ፀንቶ የሚቆየው ለአንድ አመትና ከዛ በላይ ለሆነ ጊዜ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ከአንድ አመት ላነሰ አጭር ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡-

   ሀ . አንድ አስመጪ ያስመጣቸውን ተሸከርካሪዎች እስከሚሸጥ ድረስ ላለው ጊዜ፣

   ለ . ከወደብ ወደ ሀገር የሚገባ ተሸከርካሪን በተመለከተ፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ከአስር ቀን በታች ለሆነ ጊዜ የ 3ኛ ወገን የመድን ሽፋን መስጠት አይቻልም ፡፡

4. ከአንድ ዓመት በታች ለአጭር ጊዜ ለሚሰጥ የመድን ሽፋን የአረቦ ተመን የሚሰላው በተከታዩ ሰንጠረዥ መሰረት ነው፡-

የውል ዘመን	ከአመቱ አረቦን ላይ የሚከፈል
ከ 10 ቀን እስከ 1 ወር	30%
ከ 2 ወር ለማይበልጥ	50%
ከ 3 ወሮች ለማይበልጥ	70%
ከ 4 ወሮች ለማይበልጥ	80%
ከ 5 ወሮች ለማይበልጥ	90%
ከ 6 ወሮች ከበለጠ	የአንድ አመት አረቦን

5. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ለአጭር ጊዜ ለሚሰጥ የመድን ውል ሽፋን የሚከፈለው አነስተኛው የአረቦን መጠን ከመቶ ሀምሳ ብር ማነስ አይችልም፡፡

7. የመድን ውል ስለመሰረዝ

1. የመድን ውል የሚሰረዘው ተሽከርካሪው የወደመ ወይም ከጥቅም ውጪ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለተሰረዘው የመድን ውል ቀሪ ጊዜ የሚሰላው የፈንድ ተመን ድርሻ ተመላሽ አይሆንም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ እንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ ለሶስተኛ ሰው በሽያጭ በስጦታ ወይም በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ቢተላለፍ ሽፋኑ አይቋረጥም ፡፡
4. የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ አገልግሎቱ ከተቀየረና የአረቦን ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ ልዩነቱን በአረቦን ታሪፍ መሰረት ባለንብረቱ ለመድን ሰጪ ኩባንያው ከፍሎ ሽፋኑ የአገልግሎቱ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ይቀጥላል፡፡

8. የጠፉ ወይም የተሰረቀ የመድን ምስክር ወረቀት እና ተለጣፊ

1. ማንኛውም መድን ሠጭ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ስር ያለ የመድን ምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ ወዲያውኑ ለኤጀንሲው እና ለፖሊስ ሴሪያል ቁጥር እና የጠፋበትን ቅርንጫፍ በመግለጽ ከነዝርዝር መረጃው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መድን ሠጭው ለኤጀንሲው እና ለፖሊስ ካሳወቀ በኋላ ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት እና የመድን ምስክር ወረቀቱን እና ተለጣፊውን ዋጋ በመክፈል ከኤጀንሲው ምትክ ጠይቆ መውሰድ ይችላል፡፡

9. የተበላሸ፣የተቀደደ እና ከጥቅም ውጪ የሆነ የመድን ምስክር ወረቀት እና ተለጣፊ

1. ማንኛውም መድን ሰጭ የተበላሸ ፣ የተቀደደ እና ከጥቅም ውጭ የሆነ የመድን የምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ ባጋጠመው ጊዜ ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለመድን ገቢው ምትክ እንዲሰጠው ኤጀንሲውን መጠየቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም መድን ሰጭ የመድን ምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ ላይ መረጃዎችን ሲሞላ ምንም ዓይነት የጽሕፈት ስህተት ቢያጋጥመው ሰነዱ ላይ ሁለት በጕን የተኙ መስመሮችን በማድረግ በመሐከሉ ላይ "ተሰርዟል" የሚል ጽሑፍ በማስቀመጥ ሰነዱን ለብቻ ማስቀመጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም መድን ሰጭ የተሰረዘን የመድን ምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ በመመዝገብ በተገቢው ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ለኤጀንሲው መላክ አለበት፡፡
4. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሰረት ተበላሽቶ ለተወገደ የመድን ተለጣፊ እና የመድን ምስክር ወረቀት ለመድን ሰጭው ተመላሽ የሚያደርገው ገንዘብ/ሂሣብ/ አይኖርም፡፡

10. የመድን ሰጭው ኃላፊነት

ማንኛውም መድን ሠጭ፡-

1. በኤጀንሲው የታተመ የመድን የምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ወጪ ተሠልቶ ከታወቀ በኋላ መድን ሰጭው በወሰደው ሰነድ ቁጥር ልክ ለኤጀንሲው መክፈል አለበት፡፡
2. ከኤጀንሲው የተረከባቸውን እና አገልግሎት ላይ ያዋላቸውን የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ለመቆጣጠር የሚያስችለው የተለየ የባሕር መዝገብ ማዘጋጀት ወይም

እየተጠቀመ ያለበትን የባሕር መዝገብ ለዚሁ አላማ በሚያመች መንገድ ማስተካከል አለበት፡፡

3. የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ በማለቁ ምክንያት አገልግሎት መስጠት እንዳያቋርጥ አስቀድሞ ከኤጀንሲው በመጠየቅ መዉሰድ አለበት፡፡
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 የተቀመጠው ሩብ ዓመት ካለቀ በኋላ ባለው አስር ቀን ውስጥ ለመድን ገቢዎች የሰጠውን የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ብዛት እና ዝርዝር መረጃ፣ ሲዘጋጁ በመበላሸታቸው የተሰረዙ ሰነዶችን እና የተከፈለ ካሳ እና በሂደት ላይ ያለ ካሳ መጠንና ብዛትን ከሪፖርት ጋር አያይዞ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡
5. የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው የሚያቀርበው ጥያቄ የሚፈለገውን ቁጥርና የተረካቢውን ስም በመግለፅ በመድን ሰጭው ተቋም የበላይ ሀላፊ በተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡
6. የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሠረት የሚያስፈልጉትን መረጃዎችና ሰነዶች በአግባቡ ለኤጀንሲው አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡
7. ያቀረበው የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ ይሰጠኝ ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው በኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም በወኪሉ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
8. ያቀረበው ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት ተቀባይነት ካገኘ ኤጀንሲው ለተጠየቀው የመድን ምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ አስፈላጊውን ክፍያ በመቀበል ጥያቄውን ያቀረበው መድን ሰጭ እንዲረከብ ለወከለው ሰው ያስረክባል፡፡
9. ከእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተሰበሰበው የፈንድ መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የፈንድ ገቢ ማሰባሰቢያ እና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ በመሙላትና ከሌሎች አባሪ ሰነዶች ጋር በማድረግ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡
10. የመድን ሽፋን ውል ሲቋረጥ ወይም የውል ዘመኑ ሲያልቅ መድን ገቢው የመድን ምስክር ወረቀቱንና የመድን ተለጣፊውን ለመድን ሰጪው መመለስ ያለበት ሲሆን መድን ሰጪውም የተመለሱ የምስክር ወረቀቶች እና የመድን ተለጣፊዎችን በየሩብ አመቱ ለኤጀንሲው በሪፖርት ማሳወቅ አለበት ፡፡

11.ሽፋን ባገኙ ተሽከርካሪዎች ገቢ የሆነ የአረቦን መጠን 10% ተጨማሪ የፈንድ ታሪፍ እና የተጠቀሙት የመድን ምስክር ወረቀት እና ተለጣፊ ያካተተ ዝርዝር መረጃ እያንዳንዱ ወር ባለቀ በአስር ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው በሪፖርት ማሳወቅ አለበት።

11. የፈንድ ገቢ አሰባሰብ

1. የፈንድ ገቢ ከመድን ሰጭዎች የሚሰበሰበው በቼክ ወይም በባንክ ዝውውር የክፍያ ማዘዣ ብቻ ሲሆን ኤጀንሲው የፈንድ ገቢው ገቢ የሚደረግበትን የባንክ አካውንት በመክፈት ለሁሉም የመድን ሰጭዎች ያሳውቃል።
2. ለፈንድ ገቢ አሰባሰብ ሲባል የሂሳብ ዘመኑ የሚሆነው ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ሲሆን እያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን ለአራት እኩል ወራት በሩብ ዓመት በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት ይከፈላል፡-

ሩብ አመት	የሚያካትተው ወራት
የመጀመሪያው ሩብ ዓመት	ሐምሌ፣ ነሐሴ እና መስከረም
ሁለተኛው ሩብ ዓመት	ጥቅምት፣ ህዳር እና ታህሳስ
ሦስተኛው ሩብ ዓመት	ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት
አራተኛው ሩብ ዓመት	ሚያዝያ፣ ግንቦት እና ሰኔ

3. ማንኛውም መድን ሰጭ የሰበሰበውን የፈንድ መጠን ሩብ ዓመቱ ካለቀ በኂላ ባለው 10 ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ገቢ ማድረግ አለበት ፤
4. መድን ሰጭው የሰበሰበውን የፈንድ ገንዘብ ገቢ በሚያደረግበት ወቅት ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን የፈንድ ገቢ ማሰባሰቢያና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ በመጠቀም በኤጀንሲው ወደ ተከፈተዉ አካዉንት ገቢ ማድረግ አለበት ፤
5. መድን ሰጭዉ ከፈንድ ገቢ ማድረጊያዉ መንገድና ከሪፖርት ማቅረቢያዉ ቅጽ በተጨማሪም ከዚህ የሚከተሉትን ሰነዶች በአባሪነት ማያያዝ አለበት፡-

   ሀ. የተፈረመና ማህተም የተደረገበት የመሸኛ ደብዳቤ እና

   ለ. በሩብ አመቱ ዉስጥ የተሰጡ የመድን ምስክር ወረቀቶች እና የመድን ተለጣፊዎች ዝርዝር

ሐ. የባንክ አድቫይስ፣የገንዘቡን መጠን ፣የአካውንት ቁጥሩን እና የኤጀንሲውን ስም የሚገልጽ ማረጋገጫ

6. ኤጀንሲው ለተረከበው የፈንድ ገቢ እና አባሪ ሰነዶች ተገቢውን ማረጋገጫ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡
7. ኤጀንሲው ገቢ የተደረገለትን ገንዘብ እና የተረከባቸዉን ሰነዶች ኤጀንሲው በውስጥ ባለው የአሰራር ስርአት መሠረት በመመርመርና በማጣራት ስህተት ወይም ችግር ካጋጠሙት ከሚመለከተው የመድን ሰጭ ጋር በመነጋገር ያስተካክላል፡፡
8. ኤጀንሲው ባደረገው ማጣራት በመድን ሰጭ የቀረቡ መረጃዎች ስህተት ወይም ችግር እንዳለባቸው ካረጋገጠ ስህተቱ ወይም ችግሩ በ10 ቀናት ውስጥ ታርሞ እንዲመለስ ለሚመለከተው መድን ሰጭ ያሳውቃል፡፡

ክፍል ሶስት

ተደጋጋሚ አደጋ ስለሚያደርሱ መድን ገቢዎች

12. አደጋን ስለመመዝገብ

ማንኛውም መድን ሰጭ መድን ገቢዎች የሚያደርሱትን አደጋ እና የጉዳት መጠን በተደራጀ መልኩ ለመመዝገብ የሚያስችለውን የአደጋ መመዝገቢያ ቅጽ በማዘጋጀት መመዝገብ አለበት፡፡

13. ተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ

1. ማንኛውም መድን ሰጭ ለመድን ገቢ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን ውል ዕድሳት ከማድረጉ በፊት መድን የተገባለት ተሽከርካሪ በአለፈው ዓመት የመድን ሽፋን ውል ያደረሰው አደጋ እና የጉዳት መጠን ማወቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ በአንድ የውል ዓመት ውስጥ ያደረሰው አደጋ እና የጉዳት መጠን ተሰልቶ በቀጣይ ዓመት የአረቦን ተመን ላይ ጭማሪ ይደረግበታል፡፡
3. የአረቦ ክፍያ የሚተመነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገኘው መረጃ መሰረት ቀድሞ በስሙ በተመዘገበው የአደጋ ብዛት እና መጠን መሠረት ሲሆን የጉዳት ዓይነቶች እና የአረቦን መጠኑ በምን ያህል እንደሚያድግ የሚገልጽ አባሪ ሰነድ መያያዝ አለበት፡፡

4. ማንኛውም መድን ሰጭ የመድን ውል በሚያድስበት ጊዜ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ በአንድ ዓመት ውስጥ የተመዘገበበትን አደጋ እና የጉዳት መጠን መሠረት ያደረገ አረቦን በማስላት ይሰበስባል።
5. የአረቦን ጭማሪ አሰላል የአደጋ ዓይነት እና ጉዳት መጠንን ከግምት ባስገባ ሁኔታ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሠረት ይሰላል።

14. ስለ ኃላፊነት

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ቢኖርም መድን ገቢው ለደረሰው አደጋ ኃላፊ ያልሆነ እንደሆነ የአረቦን ጭማሪ አይደረግበትም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአደጋው ተካፋይ የሆነው ተሽከርካሪ አንድ ብቻ የሆነ እንደሆነ ለአደጋው ኃላፊነት አለበት።
3. በአደጋው ተካፋይ የሆኑት ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ ኃላፊነት ያለበት ተለይቶ የሚታወቀው በፖሊስ ሪፖርት ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ዓይነት አደጋ ባጋጠመ ጊዜ የአሽከርካሪዎቹ ኃላፊነት መጠን የሚወሰነው ለአደጋው መድረስ ባላቸው አስተዋጽኦ ወይም ስህተት መሠረት ነው።

15. የአረቦን ተመን አሰላል

ተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎች የሚደርሱትን አደጋ እና የጉዳት መጠን ያገናዘበ የአረቦን ተመን ለመወሰን ስሌቱ የሚከተለዉን ሰንጠረዥ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት ።

	የአደጋው ዓይነት	የመጀመሪያ አደጋ	ሁለተኛ አደጋ	ሦስተኛ አደጋ	አራተኛ አደጋ	አምስተኛ አደጋ
1	የአካል ጉዳት					
1.1.	ቀላል የአካል ጉዳት	10%	20%	50%	80%	100%
1.2.	ከባድ የአካል ጉዳት	20%	30%	50%	80%	100%
1.3.	የሞት አደጋ	50%	75%	85%	100%	150%
2	የንብረት ጉዳት					
2.1.	ከብር 50 000 በታች	10%	20%	30%	50%	100%
2.2.	ከ50001 እስከ 100000	20%	30%	75%	100%	120%
2.3.	ከ100001 እስከ 500000	50%	75%	100%	120%	130%
2.4.	ከ500001 እስከ 1000000	60%	80%	110%	130%	140%
2.5.	ከ1 000 001 በላይ	70%	90%	120%	135%	150%

16. የአረቦን ጭማሪ የሚቆይበት ጊዜ

1. በማንኛውም መድን ገቢ ላይ ተደጋጋሚ አደጋ በማድረስ ምክንያት የአረቦን ጭማሪ የተደረገበት እንደሆነ የአረቦን ጭማሪው ለቀጣዮቹ 3 ዓመታት ጸንቶ ይቆያል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ገቢው ለቀጣዮቹ 3 ዓመታት አደጋ ያላደረሰ እንደሆነ የአረቦን ተመኑ ቀድሞ ወደ ነበረበት መጠን ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

17. መድን ሰጭ ኩባንያ ስለመቀየር

ማንኛውም መድን ገቢ የመድን ግንኙነቱን ከአንድ መድን ሰጪ ኩባንያ ወደ ሌላ መድን ሰጪ ኩባንያ በሚቀይርበት ጊዜ ቀድሞ ከነበረበት መድን ሰጪ ኩባንያ ባለፉት 3 ዓመታት መድን በተገባለት ተሽከርካሪ ስም የተመዘገበውን የአደጋ ዝርዝር የሚገልጽ መልቀቂያ ወረቀት በማጻፍ ለሚቀይርበት መድን ሰጭ ኩባንያ ማቅረብ አለበት።

ክፍል አራት
በኤጀንሲው የሚፈጸም የካሳ አከፋፈል ዝርዝር ሁኔታ

18. አደጋን የማሳወቅ ተግባር

1. መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ ማንኛውም አደጋ አደጋው ከደረሰ ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው መገለጽ አለበት።
2. መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን ማሳወቅ የሚችሉት ፦
   ሀ. ተጎጂው ወይም ከተጎጂው ወይም አግባብ ካለው አካል የተሰጠ ህጋዊ ውክልና ያለው ሰው፣
   ለ. የትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ መንግስታዊ አካል፣
   ሐ. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ ተቋም፣
   መ. አደጋውን የሚያውቅ በአደጋው ቦታ የነበረ ማንኛውም ሰው፣
3. ማንኛውም ሰው መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን ወይም የካሳ ጥያቄን በስልክ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣በደብዳቤ ወይም በኤጀንሲው ዌብ ሳይት ማሳወቅ ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው በተጨማሪ ኤጀንሲው ለዚሁ ባዘጋጀው መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ፣ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ እና የትራፊክ ፖሊስ የሚሞላው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ አማካኝነት አደጋውን ማሳወቅ ይቻላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 በተጠቀሱት መንገዶች ኤጀንሲው እንዲያውቃቸው የተደረጉ አደጋዎች ወይም የካሳ ጥያቄዎች በኤጀንሲው ወይም በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የገቢ ደብዳቤዎች አመዘጋገብና ስርጭት ሥርዓት በ1፡00 ሰዓት ውስጥ ለሚመለከተው ለመድን ኦፐሬሽን ዳይሬክቶሬት ወይም ለሕክምናና ካሳ ክፍያ ቡድን መድረስ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተመለከቱት መንገዶች አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በኤጀንሲው እንደታወቀ ጉዳዩ የተመራለት የካሳ ፈጻሚ ሰራተኛ የሚመለከተው ሰው ወይም አመልካቹ እንደአግባብነቱ መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ወይም ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያውኑ እንዲሞላ ማድረግ አለበት፡፡
7. አደጋውን ወይም የካሳ ጥያቄውን ያሳወቀው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ቅጹን ከሞላ በኋላ ይህንኑ የተሽከርካሪ አደጋ ለትራፊክ ፖሊስ ፣ለፖሊስ ወይም ለመንግስታዊ አካል በወቅቱ ማሳወቁን የሚያስረዳ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት ፡፡

19. አደጋውን ወይም የካሳ ጥያቄውን የመመዝገብ ስርአት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተጠቀሱት መንገዶች መድን በሌለው ተሽከርካሪ ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋ እንዲያውቅ የተደረገ የህክምና እና የካሳ ክፍያ ቡድን አስፈላጊውን መመሪያዎችና የሥራ ትዕዛዞችን በማከል የካሳ ጥያቄውን እንዲያስተናግድ ለከፍተኛ የካሳ ክፍያ ባለሙያ ይመራዋል፡፡
2. ከፍተኛ የካሳ ክፍያ ባለሙያው የተመራለትን ጉዳይ ከካሳ ባለሙያ ጋር በመሆን በባህር መዝገብ ላይ መዝግቦ የካሳ ማህደር በመክፈት ተገቢውን ሰነዶችና ሌሎች መረጃዎች በተመለከተ በወቅቱ ክትትል ያደርጋል ወይም እንዲደረግበት ያደርጋል፡፡
3. በአዋጁ መሰረት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው ወይም ህጋዊ ተወካዩ ወይም ሌላ አካል ያሳወቀውን አደጋ ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 እና 21 በተደነገገው መሰረት በመመዝገብ ማህደር ይከፍታል፡፡
4. በባህር መዝገቡ ላይ የተጠቀሰው የማሕደር ቁጥር ከካሳ ጠያቂው ጋር እና ከሌሎች ወገኖች ጋር በሚደረግ የጽሁፍ ግንኙነት መገለጫ ይሆናል፡፡

5. መድን በሌላቸው እና ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የተለያየ የባህር መዝገብ ይኖራቸዋል፡፡

20. መድን የሌለው ተሽከርካሪ የተመለከተ የካሳ ጥያቄ የባህር መዝገብ ይዘት

መድን በሌላቸው ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የሚመዘገቡበት የባህር መዝገብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በኤጀንሲው መዝገብ ቤት ገቢ የሆነበት ቀን፣
2. የካሳ ማህደር ቁጥር
3. መየተ/ክልል/000/ዓ.ም በሚል በአጭር የተጻፉ በሚከተለው መንገድ የሚተረጎሙ ፡-
   ሀ. መተ ፡ - መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች
   ለ. ክልል፡ - አደጋው የደረሰበት ክልል
   ሐ. 000 ፡ - የካሳ መዝገብ ላይ የተመዘገበበት ቁጥር
   መ. ዓ.ም. ፡ - ዓመተ ምህረት / ዘመን
4. የተጎጅው ስም፣ የአደጋው ቀን እና የአደጋው ቦታ
5. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ ስምና አድራሻ፣ የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር እና የተሽከርካሪው ባለቤት ስምና አድራሻ
6. አደጋውን የመረመረው የትራፊክ ፖሊስ፣ፖሊስ ወይም መንግስታዊ አካል ስምና አድራሻ
7. የካሳ ክፍያ መጠን
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚገለጸው የካሳ መጠን የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፡-
   ሀ. የተያዘ አጠቃላይ መጠባበቂያ
   ለ. አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ሐ. ሆስፒታል ሕክምና (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   መ. አካል ጉዳት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ሰ. ሞት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ረ. ሌሎች ክፍያዎች
   ሠ. አጠቃላይ ክፍያ

21. ያልታወቀ ተሽከርካሪን የተመለከተ የካሳ ጥያቄ የባህር መዝገብ ይዘት

ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የሚመዘገቡበት የባህር መዝገብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በኤጀንሲው መዝገብ ቤት ገቢ የሆነበት ቀን
2. የካሳ ማህደር ቁጥር
3. ያተ/ክልል/000/ዓ.ም በሚል በአጭር የተጻፉ በሚከተለው መንገድ የሚተረጎሙ ፡-
   ሀ. ያተ ፡ - ያልታወቀ ተሽከርካሪ
   ለ. ክልል፡ - አደጋው የደረሰበት ክልል
   ሐ. 000 ፡ - የካሳ መዝገብ ላይ የተመዘገበበት ቁጥር
   መ. ዓ.ም. ፡ - ዓመተ ምህረት / ዘመን
4. የተጎጅው ስም፣ የአደጋው ቀን፣ የአደጋው ቦታ
5. አደጋውን ሪፖርት ያደረገው ሰው፣ድርጅት ወይም ተቋም ስም፣ አድራሻ እና ምርመራ
6. አደጋውን የመረመረው የትራፊክ ፖሊስ፣ፖሊስ ወይም መንግስታዊ አካል ስምና አድራሻ
7. የካሳ ክፍያ መጠን
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚገለጸው የካሳ መጠን የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፡-
   ሀ. የተያዘ አጠቃላይ መጠባበቂያ
   ለ. አስቸኳያ የሕክምና አገልግሎት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ሐ. ሆስፒታል ሕክምና (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   መ. አካል ጉዳት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ሠ. ሞት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)
   ረ. ሌሎች ክፍያዎች
   ሠ. አጠቃላይ ክፍያ

22. የካሳ ማህደር ማቅረብ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 መሠረት የተመዘገበ አደጋ /የካሳ ጥያቄ/ ከቡድን መሪው የተሰጡ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞችን የአፈፃፀም መልስ በመያዝ ለሥራ ሂደቱ ባለቤት ውሳኔ ፣ሙያዊ አስተያየት ወይም ትዕዛዝ በ1 (አንድ) ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
2. የካሳ ማህደሩ የቀረበለት የሥራ ሂደት ባለቤት የራሱን አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ በማህደሩ ላይ ወይም እንደሁኔታው የተፃፈ ሪፖርት ማሕደሩ ውስጥ በማያያዝ ለኤጀንሲው የመድን ኦፐሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በ30 ደቂቃ ውስጥ ያቀርባል፡፡
3. የመድን ኦፐሬሽን ዳይሬክተሩም ያለውን አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ በማህደሩ ላይ ወይም እንደሁኔታው የተጻፈ ሪፖርት ማሕደሩ ውስጥ በማያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ከሥራ ሂደቱ ባለቤት ጋር በመሆን ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የካሳ ማህደሩን በ30 ደቂቃ ውስጥ ያቀርባል፡፡
4. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቀረበለትን የካሳ ማህደር በመመርመር የሕግ አስተያየት የሚያስፈልገው ከሆነ የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት ወዲያውኑ ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በውስጥ ማስታወሻ ማሕደሩን ይልካል፡፡
5. የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ለቀረበለት የሕግ አስተያየት ጥያቄ በ2 (ሁለት) የስራ ቀን ውስጥ መልስ መስጠት አለበት፡፡

23. የካሳ ጥያቄ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ

1. የካሳ ክፍያ ባለሙያ የቀረበውን የካሳ ጥያቄ በፈንድ ዓላማ ስር የሚወድቅና ኤጀንሲውን የሚመለከት መሆኑን እንዲሁም በዚህ ክፍል የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን ያጣራል፡፡
2. ቀጥተኛ ለሆኑ ጉዳዮች የካሳ ጠያቂው ተገቢውን መረጃ እንዲያቀርብ ዝርዝር መግለጫ በጽሁፍ ይሰጠዋል፡፡
3. የተወሳሰቡ ጉዳዮች ወይም አጠራጣሪ እና የማጭበርበር ተግባር እንደተፈጸመባቸው የሚያጠራጥሩ ጉዳዮች ከሆኑ ምክንያቶቹን በማሕደሩ ላይ በዝርዝር ለኤጀንሲው የካሳ ክፍያ ኮሚቴ ለአስተያየትና ውሳኔ ያቀርባል፡፡

24. በአደጋ ምርመራ ወቅት ግምት ውስጥ የሚገቡ ሁኔታዎች

1. ባልታወቀ ተሽከርካሪ ወይም የመድን ሽፋን በሌለው ተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ተጎጂ ወይም ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው የሚመለከተው የትራፊክ ፖሊስ፣ፖሊስ ወይም የመንግስት አካል የአደጋውን ምርመራ የተመለከተ ሪፖርት እንዲሰጠው በተመዘገበ ደብዳቤ መጠየቁን ማረጋገጥ።
2. የአደጋ ምርመራው ሪፖርት በካሳ ጠያቂው የቀረበ ከሆነ ሪፖርቱን የሰጠውን አካል ማረጋገጫ እንዲሰጥ በደብዳቤ መጠየቅ።
3. በጉዳዩ ወይም በአደጋው ውስብስብነት ወይም በሌሎች ምክንያቶች አጠራጣሪ ጉዳዮች ካሉ ከህክምናና ካሳ ክፍያ ቡድን መሪ ጋር በመመካከር፡-

   ሀ. የሥራ ሂደቱ ውስጥ ያለ ሠራተኛ በመመደብ የአደጋ ማጣራት ሂደቱን እንዲከናወን ማድረግ ወይም

   ለ. የግል የመድን ኩባንያ ሙያተኛ የአደጋውን ሁኔታ እንዲያጣራ መመደብ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የአደጋን ሁኔታ እንዲያጣራ ለተመደበ አጣሪ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ እንደ ሁኔታው የመድን ኢንዱስትሪውን ልምድና አሠራር ተከትሎ በድርድር ይወሰናል።

25. የአደጋ ምርመራ ወይም የማጣራት ተግባር የመፈጸሚያ ጊዜ

1. ቀጥተኛ ለሆኑ የካሳ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ደረጃ ምርመራ በ30 ደቂቃ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት።
2. የአደጋ ምርመራ ሪፖርትና የማጣራት ተግባሩ እንደ አደጋው ቦታ ርቀት ሊለያይ ቢችልም በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከ10 የሥራ ቀናት በላይ መብለጥ የለበትም።

26. ለካሳ ጥያቄው ደጋፊ ሰነዶችን ስለመጠየቅ

1. የካሳ ክፍያ ከፍተኛ ኤክስፐርት ከሕክምናና ካሳ ክፍያ ቡድን መሪ ጋር በመሆን አደጋው እንዲታወቅ ወይም የካሳ ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ምርመራ እየተካሄደ እያለ ደጋፊ ሰነዶች እንዲቀርቡ አስፈላጊ ሲሆን ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ የአንድ ወር ወይንም አስፈላጊ ሲሆን ከአንድ ወር በላይ የሚሆን የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ ይጠይቃል።

2. ኤጀንሲው ለካሳ ጠያቂዎች የላከው የመጀመሪያው ደብዳቤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካላገኘ ሁለተኛ የማሳሰቢያ ደብዳቤ የጊዜ ገደቡ ካለቀ ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ በድጋሚ ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ ይልካል::
3. የሁለተኛው የማሳሰቢያ ደብዳቤ ምላሽ ካላገኘ ደጋፊ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለሶስተኛ ጊዜ ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ ይልካል::
4. ለሶስተኛ ጊዜ በተጻፈው ደብዳቤ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ደጋፊ ሰነዶች የማይቀርቡ ከሆነ የካሳ ጠያቂዎቹን በግንባር በማነጋገር የተገኘውን ውጤት በሪፖርት መልክ ከማህደሩ ጋር በማያያዝ ለኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርና ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ መቅረብ አለበት፡፡

27. ለተጎጂዎችና ለካሳ ጠያቂዎች መልስ መስጠት

1. አደጋው በተገለጸ ወይም የካሳ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ቀን ውስጥ ኤጀንሲው ጥያቄው እንደደረሰው በማሳወቅ መቅረብ ያለባቸውን ሰነዶች በመዘርዘር በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡
2. የአደጋ ምርመራ ሪፖርትና የማጣራት ተግባር እንዲሁም የአደጋው ውስብስብነት ወይም ሌሎች አጠራጣሪ ጉዳዮች ካሉ የካሳ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ኤጀንሲው በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡
3. የካሳ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ከሆነ የማጣራቱ ተግባር እንደተከናወነ የካሳ ክፍያው በአምስት የስራ ቀን እንደሚጠናቀቅ በመግለጽ በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፤

28. የካሳ ክፍያ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. ባልታወቀ ወይም መድን በሌለው ተሽከርካሪ የደረሰ የአካል ጉዳትን በተመለከተ የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ በቀጥታ በተጎጂው አማካኝነት ወይም በተወካዩ አማካኝነት መቅረብ ይችላል፡፡
2. ባልታወቀ ወይም መድን በሌለው ተሽከርካሪ የደረሰ የሞት አደጋ ካሳ ጥያቄ በሟች መሞት ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠባቸውን ጥቅም ወራሾች በቀጥታ ወይም በተወካያቸው አማካኝነት ማቅረብ ይችላሉ ፡፡

29. የጉዳት ዓይነቶች

1. የመድን ዋስትና በሌለው ወይንም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የሚደርሱ አደጋዎች የሚከተለው ደረጃ ይኖራቸዋል፡-
   ሀ. ጊዜያዊ የአካል ጉዳት
   ለ. ዘላቂ የሆነ ከፊል የአካል ጉዳት
   ሐ. ዘላቂ የሆነ ሙሉ የአካል ጉዳት
2. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም "የሞት አደጋ" ማለት ባልታወቀ ወይም መድን ባልተገባለት ተሽከርካሪ የደረሰ የአካል ጉዳት ውጤት የሞት አደጋን ሲያስከትል ነው።
3. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም "የአካል ጉዳት" ማለት ባልታወቀ ወይም መድን ባልተገባለት ተሽከርካሪ በተጎጂ አካል ላይ የደረሰ ማንኛውም ጉዳት ነው።
4. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም "ጊዜያዊ የአካል ጉዳት" ማለት ተጐጂው በደረሰበት አደጋ ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የተለመደ ሥራውን ለማከናወን እንዳይችል የሚያደርገው የአካል ጉዳት ነው።
5. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም "ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት" ማለት ጉዳት የደረሰበት ተጐጂ የተለመደ ሥራውን የመሥራት ችሎታው በዘላቂነት የሚቀንስ እና የማይድን ጉዳት ነው።
6. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም "ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት" ማለት ጉዳት የደረሰበት ተጐጂ በአካሉ ማንኛውም ክፍል ላይ የደረሰ የማይድን ጉዳት ነው።

30. ለአካል ጉዳት እና የካሳ ጥያቄ መቅረብ ያለባቸው ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ለጊዜያዊ የአካል ጉዳት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
   ሀ. የህክምና ምስክር ወረቀት
   ለ. ሐኪም መድሐኒት ያዘዘበት ማስረጃ
   ሐ. መድሐኒት የተገዛበትና የህክምና ወጪ ህጋዊ ደረሰኝ
   መ. የገቢ መጠን መግለጫ
   ሠ. ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ
   ረ. የፖሊስ ሪፖርት

The Federal Democratic Republic ... Transport
ARCHIVE

2. ለዘላቂ ከፊል ወይም ሙሉ የአካል ጉዳት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሕክምና ቦርድ ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ለሞት አደጋ የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ. የአሟሟቱን ሁኔታ የሚገልጽ የአስክሬን ምርመራ የሐኪም ማስረጃ፣

ለ. የሕጋዊ ወራሾች የፍርድ ቤት ውሳኔ፣

ሐ. የወራሾች ከሟች ጋር ያላቸው ግንኙነት እና የዕድሜ ማረጋገጫ ሰነድ፡፡

መ. የሟች ገቢ መጠን

ሠ.የሟችና ወራሾች መታወቂያ

ረ. የፖሊስ ሪፖርት

4. ለወደፊት የሚደርሱ የአካል ጉዳቶችን ተጎጂው የሚያረጋግጠው በማስረጃ ሲሆን ተጎጂው የደረሰበትንና ለወደፊት የሚደርስበትን ጉዳት ህጋዊ ማስረጃ በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት፡፡

31. የጉዳት ካሳ አተማመን

በጉዳት ዓይነቶች የካሳ አተማመን ውስጥ የሚከተሉት ጉዳዮች መታየት አለባቸው፡-

1. ግልጽ የሆኑ እና የደረሱ ጉዳቶች የካሳ መጠን ለመወሰን የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ለህክምና ያወጣው ወጪ፣ የገጠመው የገቢ መቋረጥ እና ሌሎች ወጪዎች፡፡
2. ግልጽ የሆኑ እና ወደፊት የሚደርሱ ጉዳቶች የካሳ መጠን ለመወሰን ተጎጂው የሚያጣው ገቢ ወይም የሚያወጣው ወጪ እና ዘላቂ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ያስከተለው ጉዳት፡፡
3. ተገቢው ማስረጃዎች ከቀረቡ በኋላ የካሳ ጥያቄው ተቀባይነትን ካገኘ የካሳ ፈጻሚው ከሕክምናና የካሳ ክፍያ ቡድን መሪ እና ከመድን ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር በጋራ በመመካከር ያገኘው ውጤት ላይ በመመርኮዝ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ያለውን አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ የያዘ አጭር ሪፖርት በማዘጋጀት የካሳ መጠኑ እንዲጸድቅለት ለካሳ ክፍያ ኮሚቴ ያቀርባል ፡፡
4. የካሳ ክፍያ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተተመነውን የጉዳት ካሳ መጠን ካጸደቀው የካሳ ክፍያ ቡድን መሪ የጉዳት ካሳ መጠኑን እና የተመኑ መጠን የተሰላበትን መንገድ ለተጎጂዎች በግልጽ ያስረዳል፡፡

The Federal Democratic Republic ... Ministry of Transport
ARCHIVE